# ኮቪድ-19 ወረርሽኝን በገንዘብ ድጋፍ ለመከላከል ማቀድ

# ሚያዝያ 2013፣ በየጊዜው የሚሻሻል

---

ይህ በ ኮቪድ 19 ወረርሺኝ ወቅት የመከላከያ ውጤቶችን ለማምጣት የጥሬ ገንዝብና ቫውቸር እርዳታ (CVA) መመሪያ የተዘጋጀው በዓለም አቀፍ የመከላከል ስብስብ (GPC) አባላት አስተዋጽኦ በገንዘብና መከላከያ ግብረ ቡድን የተዘጋጀ ነው። መመሪያው ለዓለም አቀፉ የመከላከል ጉድኝትና በመከላከል ላይ ለተሠማሩ ባልደረቦች ሁሉ በቅርብ እንደሚገኝ ፈጣን የማጣቀሻ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ባለሙያዎች ከተፈናቃሉ ወገኖች ወይም ደንበኞች ጋር በቀጥታ በሚሠሩበት ጊዜ ለመከላከል ስኬቶች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍን ከሌሎች ጋር በትብብር ለመሥራት ያግዛል። መመሪያው የሚያካትታቸው ነገሮችም **(1) CVA በመከላከል ሴክተሩ ውስጥ ለስኬቶች የሚደረግ የገንዘብና ቼክ ድጋፍን እና ፣ (2) በመከላከል ሴክተሩ ውስጥ የሚገኝ CVA ስኬት የገንዘብ ድጋፍ ደህንነቱ በተጠበቀ መንግድ ማዳረስን** ናቸው። ይህ ሰነድ በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድና መጠነ ርዕይውም (ሽፋኑም) ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ እንደሚሄድ ታልሞ የተሠራ ነው። ሰነዱ መነበብ ያለበትም ከሁሉም የዓለማቀፍ መከላከል ስብስብ (GPC) የኮቪድ-19 መመሪያዎች (Global Protection Cluster COVID-19 guidance)፣ ማለትም ዓመስ የኮቪድ-19ን ምላሽና ለመዘጋጀት የተወሰዱትን ተያያዥ እርምጃዎች - የመከላከል መርሃግብር መመሪያ (Protection Programming Guidance) እና እንዲሁም ነባሩን አጠቃላይ የገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሠረተ መከላከል (Protection in Cash-Based Interventions) ከሚሉት መመሪያዎች ጋር ተያይዞ ነው፡

---

| |
|---|
| ***ገንዘብ ለ መከላከል*** *የሚለው መጠሪያ የመከላከል ስኬትን ከግብ ለማድረስ ሲባል የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍን የሚገልጽ ነው።* |

## ኮቪድ-19 እና በገንዘብ ድጋፍ የመከላከል CVA ቁልፍ ግምት ውስጥ የሚገቡጉዳዮች

**CVA የመከላከል ስኬቶችን በሚከተሉት መልኮች የመደገፍ አቅም አለው:**

- ከሌሎች የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታዎች/ድጋፎች ይልቅ በፍጥነትና በዝቅተኛ ወጪ እርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች መድረስ፤
- ለጥቃት መዳረጋቸውን የተናገሩና በኮቪድ-19 ምክንያት ደህንነታቸው አደጋ ላይ የወደቁና ለማገገም መሠረታዊ አገልግሎችን ሳይቀር ማግኘት ያልቻሉ ግለሰቦችን መደገፍ፤
- ተቀዳሚ የገቢ ምንጭ የሆነው ግለሰብ./ቤተሰብ ራሱን ያገለለባቸውን/ማህበራዊ ርቀቱን እንዲጠብቅ የተደረገባቸውን፣ እና/ወይም መተዳደሪያ ገቢያቸውን እና/ወይም የገቢ ምንጫቸውን ያጡ እና ወደ መጥፎ ተግባራት (ለምሳሌ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ፣ የወሲብ ንግድ ወዘተ. ) የመሠማራት ወይም ከመኖሪያቸው የመፈናቀል/የመባረር አደጋ የተጋረጠባቸውን ግለሰቦችን/ቤተሰቦችን መደገፍ፤

- ከኮቪድ-19 ችግር ጋር ተያይዞ በተደረገ የእንቅስቃሴ ማዕቀብ/ገደብ ምክንያት በሚከሰት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የአእምሮ ጤና መጨናነቅ ሳቢያ በቤት ውስጥ የሚደርስ ጥቃት ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፤
- በቤተሰብ መለያየት ምክንያት ህፃናትን ጨምሮ ተጨማሪ ሰዎችን በቤታቸው ውስጥ በጥገኝነት የሚደግፉ ቤተሰቦችን ማገዝ፤
- የማኅበራዊ ትስስሮችንና መረደጃ ሥርዓቶችን ጠብቆ ማቆየት- የተገለሉ ግለሰቦቸችን ከጥቃት ለመከላከል የሚያግዙ፣ ለምሳሌ ተለያተው የሚኖሩ ቤተሰቦች ( አሳዳጊዎች ከህጻናት ተለይተው የሚኖሩ ከሆነ) በቀላሉ መገናኘት የሚያስችሏቸው (የመገናኛ መሣሪያዎችን ለመግዛት ወይም የስልክ ሂሳብ ለመሙላት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግን የመሳሰሉ)፣ እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችንና የጤና ባለሙያዎችን የመሳሰሉ ለሰብአዊ ድጋፍ አገልግሎት የተሰማሩ ሠራተኞችን መደገፍ፤
- የሰብአዊ ድጋፍ ተግባራትን ከወትሮው በበለጠ በመጨመር አስቀድም በነበሩ በጾታና ዕድሜ ልዩነቶች እንዲሁም በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ሊስተጓጎሉ የሚችሉ አገልግሎቶች ምንም ጉዳት ሳያደርሱና ተጎጂ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ አድርገው እንዲያልፉ ዕድል መፍጠር፤

**በኮቭድ-19 ምክንያት ለሚሰጥ የመከላከል ስኬት የገንዘብ ድጋፍ መሆን ያለበት፡-**

- በኮቪድ-19 ችግር ውስጥ ሊደረግ የሚገባው የገንዘብ ድጋፍ አደጋና ጥቅሞች ከግንዛቤ ባስገባ ትንተና ላይ ሊመሠረት ይገባል። ይህ ትንታኔ ሊደረግ የሚገባውም የተጎዱ ግለሰቦች ራሳቸው ለይተው በሚያመለክቷቸው ፍላጎቶችና ጥቅሞች ላይ ነው። ከድጋፍ ተቀባዮች ጋር የሚደረግ ምክክር አስፈላጊ የማህበረሰብ ጤናን ለመጠበቅ የተቀመጡ የጥንቃቄ መምሪያዎችን ተከትሎ መሆን ይገባዋል፤ ከተቻለም በርቀት ሊደረግ ይገባል።
- ለመከላከል ስኬት በሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ትግበራ፣ አስቀድሞም የነበሩትን ስጋቶችና ጥቃቶችን እንዲሁም በኮቪድ-19 ምክንያት የተባባሱና የተፈጠሩ ስጋቶችና ጥቃቶችን (ለምሳሌ የክፉ ቀን ማሳለፊያ ተብለው የሚደረጉትን፣ የህፃናት ብዝበዛን፣ የወሲብ ብዝበዛንና የወሲብ ጥቃትን) ለይቶ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። እነዚህም ከራሱ ከበሽታው ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶችን እንዲሁም የበሽታውን ስርጭት ለመቀነስ ከሚደረጉ (ከማይደረጉ) ተግባራት ጋር የተያያዙ ስጋቶች ሊሆኑ ይችላሉ።
- ጠንካራ ትንታኔ ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል። ትንታኔው የአውድ ፣ የስልጣን/አቅም፣ የጾታ፣ ትንታኔ ማድረግና እና እርስ በርስ የሚጠላለፉ የማንነት ገጽታዎች (ለምሳሌ ዕድሜ፣ ወሲባዊ ዝንባሌን፣ ችሎታ፣ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት እና የዘር ሀረግ) እንዴት መገለልን፣ መድልዎን፣ ጭቆናን፣ ተቋርጦ መቅረትን እና ከለላ የማጣትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉና የገንዘብ ድጋፉ ለእንዲህ አይነት የጥበቃ/እንክብካቤ ጉዳዮች እንዴት መፍትሔ ሊያመጣ ወይም ሊያባብስ እንደሚችል፤ እነዚህ ስጋቶችና ጥቃቶች እንዴት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የበለጠ የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የባሰ ተጠቂ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ማሳየት አለበት። ይህ ትንታኔ ‹‹ለጥቃት የተጋለጡ›› የህብረተሰብ ክፍሎችን ከመለየት ያለፈ ትንታኔ መሆን አለበት።
- ለችግር የተጋለጡ የኅረተሰብ ክፍሎችን ተደራሽነት የሚያደናቅፉ እንቅፋቶችን ባስወገደና የበሽታውን ስርጭት ለማቆምም በተቻለ መጠን የሰው ከሰው መገናኘትን በቀነሰ መንገድ መተግበር አለበት። አማራጭ የዲጂታል እና የርቀት ግንኙነቶች፣ ለምሳሌ እንደ ሞባይል ገንዘብ ወይም ስልክ መር የድጋፍ አገልግሎት የመሰሉ የበሽታውን ስርጭት ሊቀንሱ የሚችሉ ስልቶች ሊተገበሩ ይገባል።
- ለእንክብካቤ የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፍ አላላኮች ተቀባዮችን ለተጨማሪ ጉዳትና ችግር ሳይደርጉ ለታለመላቸው ተጠቃሚዎች ጥበቃ ብቻ መድረሳቸውን በሚያረጋግጥ መልክ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል። የተለዩ ጠቀሜታወችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የቁጥጥር ስልቶችን በፕሮግራም የቁጥጥር ሂደት አካል እና በድኅረ-ሥርጭት ቁጥጥር (PDM) ወይም በተመሣሣይ የቁጥጥር መንገዶች ውስጥ ማካተት ማድረገ ይገባል።

Global Protection Cluster

## ቁልፍ ተግባራት፡- ጥበቃ በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች ሁሉ CVA ስኬት የገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀም

- ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን አካላት ለመለየት ዘርፈ ብዙ መንገዶችን መጠቀም። ለምሳሌ በሚመለከታቸው አካላት በሚቀርብ ምክረ ሀሳብ፣ በውሃና ንጽህና አቅራቢ ተዋናዮች (WASH) በጤና ዘርፍ ባለሙያዎች፤ ከነባር የማህበረሰብ መረዳጃ ትሥሥሮች ምክረ ሃሳብ. ምክር መስጫ የስልክ መስመሮች እና የአካል ጉዳተኞች ድርጅቶች፤
- አዎንታዊ ስኬት ለማምጣት ላይ ያለሙ የገንዘብ ድጋፎች ሁልጊዜም መነደፍ ያለባቸው በሰፊ የጥበቃ ፕሮግራም በተካተቱ አውድ-ውስን አካላት ሆነው ነው። ለምሳሌ አንድ የድጋፍ ሰጪ ባለሙያ ከገንዘብ ድጋፍ አቅራቢው ጋር በመተባበር እንደሚከውነው አንድ ውስን ክስተት ክትትል (ማኔጅመንት) ወይም እንደ ሌላ የተለየ ተግባር ሆነው ሊካተቱ ይችላል።
- በኮቪድ-19 ችግር ወቅት ሊያጋጥሚችሉ የሚችሉ ተጋላጭነቶች እና ስጋቶች ላይ የተመሠረቱ የተጋላጭነት መሥፈርቶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።
- የገንዘብ ድጋፍ ለችግር ለተጋለጡ ግለሰቦች ጠቀሜታ የሚኖረው መሆንና አለመሆኑን፣ እና ድጋፉ በገንዘብ፣ በቫውቸር ወይም በአይነት ሲሰጥ ሊመጡ የሚችሉ አደጋዎችን ማወዳደር፤ ወይም ደግሞ ምንም አይነት ቁሳዊ ድጋፍ ሳያደረጉ ድጋፉን በቅስቀሳና በአገልግሎት መልክ ብቻ በማቅረብ የሚገኘውን ጠቀሜታ ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል። እያንዳንዱን የድጋፍ ጥያቄ እንዴት መካተት እንዳለበት እና ከሩቅ ቦታ የሚመጡ የድጋፍ ጥያቀዎችን በስልክ አማካኝነት (የኔትወርክ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር) እንዴት መገምገም እንዳለባቸው ማሰብ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ፣ ግምገማውን ከፍተኛ ጥራት ያለው የአየር ማስገቢያ (ቬንቲለተር) ባለበት ህንጻ ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ ደህንነቱ በተጠበቀና ዘዋራ በሆነ ሥፍራ ማድረግ ማድረግ ይገባል።
- የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ፣ ለኮቪድ-19ም ሆነ ለሌላ ለማንኛውም አይነት ድጋፍ ለመስጠት ለሁሉም ሊስማማ የሚችል አንድ አይነት የአከፋፈል/አሰጣጥ ስልት፣ መጠን፣ የጊዜ ርዝመት እና ድግግሞሽ አይኖርም። እያንዳንዱ የድጋፍ አሰጣጥ መንገድ የተለያዩ ተፈጥሮ ላላቸው ድጋፍ ፈላጊዎች ድጋፉን ለማድረስ አስተማማኝና ተስማሚ መሆን ይኖርበቸዋል። ይህም ማለት ቋሚና በድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችና በገንዘብ ድጋፍ አቅራቢዎችም የጋራ አመራር የተመሠረቱ የድጋፍ አሰጣጦች ሊኖሩ ይገባል።
- ለተጎዱ ሰዎች የገንዘብ ድጋፍ የሚቀርብበት መንገድ፣ ተቀባዮች ድጋፉን ለመቀበልና ለመጠቀም ሲሉ ከቤታቸው የሚወጡበትን ሁኔታ መቀነስ አለበት። በእድሜ የገፉ ሰዎች፣ የአካል ጉዳተኞች እና የተለያዩ የጤና እክሎች ያሉባቸው ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፉን ለመቀበልና ለመጠቀም በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ለከፋ ህመምና ለሞት የመጋለጥ ዕድላቸው የጎላ ነው። ተረጂ ተኮር የሆኑ፣ ማንነትን የማያጋልጡና ምስጢራዊነትን የጠበቁ የቤት ለቤት ዕደላዎች ተቀዳሚ ተመራጭ ሊሆኑ ይገባል። የሚቻል ከሆነ የሰዎችን አካላዊ መቀራረብ የማይሹ በሞባይል እንደሚላክ ገንዘብ አይነት ድጋፍ ማቅረቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ሊውሉ ይገባል።
- የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበት ጊዜና ሰዓት ሲታሰብ ጾታዊ ጉዳዮችን ከግምት ማስገባት ይገባል (ለምሳሌ የሴቶችና የወጣት ሴት ልጆች ለገበያና ለቴክኖሎጂ ያላቸው ቀረቤታ፣ የመንቀሳቀስ ነጻነት፣ በቀኑ ውስጥ እንክብካቤ ለማድረግ የተወሰኑ ጊዜያት፣ የሰዓት እላፊ ወዘተ.)

Global Protection Cluster

- የገንዘብ ድጋፍን ለመከላከል ስኬት ለመጠቀም፣ ተገቢ የገንዘብና የሰው ሀብታ ያስፈለልጋል- በመሆኑም አስቀድሞ በሚዘጋጅ የገንዘብ ዕቅድና እና የሰው ኃይልን የሚመለከት ውሳኔዎች ለመከለከል ስኬት የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍን ማካተት ይገባል።
- ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ለማሰልጠን አስፈላጊ ሀብትና ጊዜ መኖሩን ማረጋገጥ ይገባል (በርቀት ሚደርግ የአቅም ግንባታ፣ የርቀት ክትትል፣ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ወዘተ. ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።)
- ለመከላከል የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መረጃን በሚመለከት የመረጃ ጥበቃን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፤ እንዲሁም መረጃ ማካፈልንና ማከማቸት በሚመለከተው ፕሮቶል መሠረት መከናወኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።
- የመረጃ ሥርጭት በሁለንተናዊ መርሆች መሠረት ሊዘረጋናና በተቻለ መጠን ሁሉንም አካታችና በብዙ የአቀራረብ ስልቶች (ሞዳሊቲስ) ሊቀርብ ይገባል። በዕድሜ የገፉ ሰዎች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የንዑስ ቋንቋ ተናጋሪዎች የገንዘብ ደጋፍ መረጃን ለማግኘት ተግዳሮት ሊኖርባቸው ስለሚችል ተቋርጠው ሊቀሩ ይችላሉ።
- በወረርሽኙ ምክንያት የተባባሰ ማኅበራዊ ውጥረት ስጋትነ ለመቀነስ ተቃርኖን ከግምት ያስገባ አካሄድ መከተል ያስፈልጋል።

## የመከላከል ትኩረት ዘርፎች - ለጥቆማ ያህል

**ጾታ ተኮር ጥቃት Gender-based Violence (GBV):**

- በፆታ ተኮር ጥቃት የሰለጠኑ ባለሙያዎች (ለምሳሌ የጉዳይ ሠራተኞች) የገንዘብ ድጋፍ ፆታ ተኮር ጥቃቱን እንዴት ሊቀርፍ እንደሚችል እያንዳንዱን ንጥል ክስተት አንድ በአንድ እንዲገመግምና መፍትሔ እንዲሰጥበት ማድግ ያስፈfልጋል፤ በየጊዜው የፆታ ተኮር ጥቃት ሰለባዎችን ፍላጎትና ስጋት ይገምግሙ እና ስፈላጊ ከሆነም ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግበትን ውሰኔ ያስተላልፉ።
- በፆታ ተኮር ጥቃት ( ማለትም በቅርብ ወዳጅ/አጋር የሚደርስ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ የወሲብ ብዝበዛና ትንኮሳ ወዘተ.) ምክንያት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ፣ አውድ-ውስን ለሆኑ ፆታ ተኮር ጥቃቶች ድጋፍ ለማድረግ ከተያዙ አገልግሎቶች ውስጥ (ለምሳሌ የነጠላ ጉዳይ ክትትል፣ ብቃት ያለው አገልግሎት አቅርቦት፣ የባህርይ ለውጥ አምጪ ተግባራት፣ የፖሊሲ ቀረጻ እና የመብት ሙግት) ጋር ተካትቶ እንዲሰጥ ያድርጉ፤
- የገንዘብ ድጋፍ የማቆም ውሳኔ ሲደረግ የፆታዊ ጥቃት ባለሙያዎችና የገንዘብ ድጋፍ አቅራቢዎች በጋራ ሆነው ስለያንዳንዱ ጉዳይ አንድ ባንድ ተመልክተው በሚደርሱበት ስትራቴጂ መሠረት እንዲሆን ያስተባብሩ፤
- በያንዳንዱ ድጋፍና አገለግሎት ውስጥ ለፆታ ተኮር ጥቃት የቀረበውን የገንዘብ ድጋፍ ስኬት በጥንቃቄ ይከታተሉ። የስኬቱ ክትትልም እንደ ፕሮግራሙ ተገቢ አላማዎች ትኩረት ማድረግ ያለበትም በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይገባል፡- ለፆታ ተኮር ጥቃት የመጋለጥን ስጋት መቀነስ ( ለምሳሌ በቅርብ ወዳጅ/አጋር የሚደርስ ጥቃትን መቀነስ)፣ ለፆታዊ ጥቃት የሚያጋልጡ አማራጮችን ማስቀረት (ለምሳሌ ሴተኛ አዳሪነትን ከችግር መውጫ መንገድ አድርጎ መቁጠርን መቀነስ ወይም ከቀደመው በተሻለ ደህንነቱ የተጠበቀ የሴተኛ አዳሪነት ህይወት እንዲኖራቸው ማድረግ)፣ ወይም የተለያዩ አገልግሎቶችን ማቅረብ (ለምሳሌ የተሸሻሉ የሥነተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ማቅረብ)። ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸcው ጉዳዮች ( ለምሳሌ ከመጀመሪያ የተጠቀሱት ሁለቱ) ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡት በጉዳዩ ላይ ዋና ተጠሪ በሆነው ሠራተኞችና በሰለጠኑ የፆታ ተኮር ጥቃት ባለሙያዎች ነው።
- ስለጾታዊ ጥቃት የሚተላለፉ መልዕክቶች ሁሉ መሰራጨት ያለባቸው የጾታ ተኮር ጥቃት ድጋፍ አገልግሎቶች በተዳረሱባቸው ቦታዎች ብቻ ነው፤ መልእክት የሚተላለፍበትን መንገድ/ዕቅድም ከፆታ ተኮር ጥቃት

Global Protection Cluster

ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ያዘጋጁ። ለፆታ ተኮር ጥቃት የሚደረግ ድጋፍን የሚመለከት መረጃ ለማሰራጨትና እና አስተማማኝና ተደራሽ አገልግሎት አሰጣጥን የሚመለከት ግብረ መልስ ለመሰብሰብ፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የድጎማ መስጫ ፕሮግራሞች እንደ መነሻ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

- *ከዚህ በላይ ቀረበው ሃሳብ የተወሰደው ከ The Cash and GBV Compendium እና ከ GPC-IASC Identifying & Mitigating Gender-based Violence Risks within the COVID-19 Response Tip Sheet ነው።* *በተጨማሪም የፆታ ጥበቃ ጉድኝት* (GPC)ን Gender-Based Violence And Cash-Based Interventions Tip-Sheet ይመልከቱ።

**የህጻናት ጥበቃ Child Protection (CP):**

- ለሕጻናት ጥበቃ ስኬት የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በሚገባ በሰለጠኑ ህጻናት ጥበቃ ሠራተኞች (ለምሳሌ የጉዳዩ ሠራተኞች) የሚመራ መሆኑን ያረጋግጡ፤ እንዲሁም እያዳንዱ ጉዳይ በተናጠል በመለየትና በመገምገም የገንዘብ ድጋፍ እንዴ አድርጎ የህፃናት ጥበቃውን ሊታደግ እንደሚችል ይመርምሩ።
- በየጊዜው ለእየንዳንዱ ህጻን እና በቤተሰብ ደረጃ የሚያስፈልገውን የህጻናት ጥበቃ ፍላጎትና ስጋት ይገምግሙ።
- የገቢ ምንጫቸው በኮቪድ-19 ምክንያት ለቀነሰባቸውና ህጻናት ለሚገኙባቸው ቤተሰቦች ጎጂ የሆኑ አማራጮች ላይ መተማመንን ለመቀነስ የገንዘብና የምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ ያድርጉ።
- ምስጢራዊነትን በጠበቀ መንገድ (በማንና እንዴት የሚለው በግልጽ ሳይታወቅ) የህጻናት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች የገንዘብ ድጋፍ ወደሚሰጡ አካላት ይምሩ። አስፈላጊ ከሆነም ይህን ተግባር በኮቪድ-19 ችግር ውስጥ የህጻናት ጥበቃ ንጥል ጉዳይ ክትትል(ኬዝ ማኔጅመንት) (በዝጅት ላይሚገኝ) መሠረት ከየድርጅቶች መመሪያዎች ጋር በማጣመር ማከናወን ይቻላል።
- በየአውዱ ያሉ የህጻናት ጥበቃ አካሄዶች በዚህ ወረርሽኝ ወቅት ስለሚለወጡ በየጊዜው ይከታተሉ። ከገንዘብ ድጋፍ አቅራቢዎች ጋር በትብብር በመሥራት በድጋፉ ሊካተቱ የሚገባቸውን አዳዲስ ቦታዎች ወይም ተጨማሪ መስፈርቶችን በማካተት በነባር ተተኳሪ ቦታዎች ላይ ሳይካተቱ የቀሩ ካሉ በገንዘብ ድጋፍ እንዲካተቱ ያድርጉ። ።
- በያንዳንዱ ጥቅል ድጋፍና አገለግሎት ውስጥ ለህጻናት ጥበቃ ስኬት የቀረበውን የገንዘብ ድጋፍ በጥንቃቄ ይከታተሉ። የክትትሉ ትኩረት ማድረግ ያለበት የህጻናትን የአደጋ ተጋልጡ በመቀነስ ላይ (ለምሳሌ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ. ጥቃት መቀነስ ወዘተ.) መሆን አለበት።

ለኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንዲስማሙ ተደርገው የተወሰዱ ሌሎች የህጻናት ጥበቃ ላይ ያተኮሩ ጉዳዮች ከህጻናት ጥበቃ ጥምረት (CP Alliance) ገጽ፡ Protection of Children during the COVID-19 pandemic ማግኘት ይቻላል። እንዲሁም ለተጨማሪ ነጥቦች የፆታ ጥበቃ ጉድኝት (GPC)ን Child Protection and Cash-Based Interventions Tip-Sheet ይመልከቱ።

**ቤት፣ መሬትና ንብረት Housing, Land and Property (HLP):**

- ከመኖሪያ መፈናቀልን ለማስቀረት ለአጭር ጊዜ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማቅረብ ይገባል። ከመኖሪያ መፈናቀል አንዴ ከተከሰተ በኋላ በመፈናቀልና-ማፈናቀል ሂደቱ ወደተሳተፉ አካላትና ወደሌሎች ቤተሰቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ በመዛመት ተጨማሪ መፈናቀልን ሊያስከትልና ሊያባብስ ይችላል።

- የገንዘብ ድጋፍ መሰጠት ያለበት ለተቋረጡ አቅርቦቶች ነው፤ ጠቅላላ የቤት አስቤዛን በክፍያ ማስቀጠል ስለማይቻል።
- የሚደረገው ድጋፍ፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ በተቻለ ፍጥነት በአካባቢው የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ ቁሳቁሶችን፣ አቅርቦቶችንና መሠረተ ልማቶችን በመጠቀም የራሱን በቂ መኖሪያ የማግኘት መብት ለመጠቀም የሚያስችል መሆን ይኖርበታል።
- ተከራይተው ለሚኖሩ ሰዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ከመረጃ፣ ከምክር እና የህግ አገልግሎት ጋር ሊቀርብ ይገባል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከአከራዮችና የመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር ከሚደረግ ከመኖሪያ ማፈናቀለልንና የአገልግሎት መቋረጥን ለመመለስ ከሚደረግ ቅስቀሳ ጋር የተጠመረ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል።
- ተፈናቃዮችን ወደ ሌላ በታ ወስዶ ማስፈር የመጨረሻ አማራጭ ተደርጎ ነው መወሰድ ያለበት። ይህ መደረግ ያለበትም በፈናቀሉን ማስቀረት የማይቻል ሲሆንና ግለሰቦች ባሉበት በታ መቆየታቸው ለህይወታቸው አስጊ ከሆነ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ ለአስቸኳይ ጊዜ የሚሆን ማረፊያ እና የገንዘብ ድጋፃም ማዘጋጀተ ያስፈልጋል።
- መፈናቀልን ተከትሎ በውርስ ክርክርና በኮቪድ-19 ሞት ምክንያት አስቸኳይ የገንዘብ እርዳታ፣ የምክርና የህግ አገልግሎት ፍላጎት እንደሚኖር መጠበቅ ያስፈልጋል።

ከዚህ በላይ የቀረበው ይዘት እንዲሰመማማ ተደርጎ የተወሰደው ከ *HLP in COVID - Global HLP AOR (Working Document)* እና ከ*GPC HLP and CBI Tip Sheet* ነው።

## ቁልፍ ተግባራት፡- ለመከላከል ስኬት ከሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ ስጋቶችን መለየትና መፍትሔ መስጠት

የገንዘብ ድጋፍ በተፈጥሮው ከሌሎች የድጋፍ አይነቶች (ለምሳሌ በዓይነት ከሚደረግ ድጋፍ) የበለጠ ለስጋት የሚያጋልጥ አይደለም። ከገንዘብ ድጋፍ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ስጋቶች የሚመነጨት ድጋፉ ከሚደረግበት ዐውድ፣ ዕድሜ፣ ፆታ እና የህብረተሰብ ስብጥር ጋር ተያይዞ ነው። በመሆኑም ከገንዘብ ድጋፍ ጋር ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን አስቀድሞ መለየት፣ ስጋቶችን መቅረፍ እና የተለዩ የስጋት ምንጮችን መከታተል፣ የመቅረፊያ መንገዶችን ውጤታማነትም መከታተል፣ የድጋፍ ተቀባይ ሰዎችን ተጠቃሚነትና ለጉዳት አለመዳረግን ያረጋግጣል።

ስጋቶችን ለመቀነስና ጠቀሜታዎችን ለመጨመር የሚከተሉትን መተግበር ያስፈልል፡-

- ግምገማዎችን፣ ልየታዎችን፣ አሠራሮችን፣ አተገባበሩን፣ ክትትሉን እና ተጠያቂነትን በዕድሜ፣ በፆታ፣ እና በስብጥር መነጽር መመልከት፤
- የገንዘብ ድጋፍ በግለሰቦች፣ በቤተሰቦች፣ በማህበረሰቡ ላይ የሚያስከትለውና የሚያባብሰው የአደጋ ስጋት ነው እና ጠቀሜታ የሚለውን ከግንዘቤ ማስገባተ ያስፈልጋል። የሚያጋጥሙ አዳዲስ ስጋቶችንስ እርዳታ የሚደረግላቸው ግለሰቦች. ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች፣ የሰበብአዊ እርዳታ ድርጅቶች እነ ሌሎች ሃላፊነት ያለባቸው አካላት (መንገግትም ጭምር) እና/ ወይም ችግሮችን ለመቅረፍ በፕሮግራም መልክ የታሰቡ ተግባራት ምን ያህል ሊቀርፏቸው ይችላሉ የሚለውንም ማሰብ ይገባል።
- የገንዘብ ድጋፉ በገንዘብ፣ በቫውቸር ወይም በአይነት ወይም ደግሞ ምንም አይነት ቁሳዊ ድጋፍ ሳያደረጉ ድጋፉን በቀስቀሳና በአገልግሎት መልክ ብቻ በማቅረብ የሚገኘውን ጉዳትና ጠቀሜታ ከግምት በማስገባት ማወዳደር ይገባል ።

Global Protection Cluster

- የገንዘብ ድጋፍ ማድረጉ ተመራጭ ከሆነ፣ የስጋት መቅረፊያ መንገዶችን መዘርጋት እና የሚቀርበውን የድጋፍ አይነት ተለዋዋጭ በማድረግ (በገንዘብ ድጋፍ/ ወይም በዓይረት)፣ ድጋፉ የሚቀርብበትን መንገደ ለዋዋጭ በማድረግ ( በሞባይል ገንዘብ፣ ገንዘብ በእጅ ክፍያ) ማካሄድ ከአቅርቦት ሰንሰለት፣ ከዋጋ ንረት ከጸጥታና ደህንነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ከመቅረፉም ባሻገር በተለየAዩ ምክንያቶች ሊለዋወጥ ከሚችለው የተጠቃዎች ምርጫ ጋርም ድጋፉን ለማስማማት ይጠቅማል።
- የገንዘብ ድጋፍ አቅራቢናና የደህንነት ጥበቃ ባልደረቦች በአንድ ላይ ሊሠሩና አስፈላጊ ከሆነም በአካባቢው፣ በሀገር፣ በቀጠና እና በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከሚሠሩ ቡድኖች ጋር ግንኙነት መፍጠርና በተለይ በግምገማ፣ በአሠራር ዝርጋታ፣ በክትትልና ቁጥጥር ጊዘ  መተባበር እንዲሁም የመፈጸም አቅማቸውን በማሳደግ ይገባቸዋል። በየፕሮግራሙ ዑደት ሁሉ ቢያንስ አይቀሬዎቹ የደህንነት ከለላ ጥያቄዎች ሊካተቱ ይገባል።
- የገንዘብ ድጋፍ አድራጊ ባለደረቦችንና አጋሮቻቸውን ፆታዊ ትንኮሳሳ ብዝበዛን ስለመከላከል፣ ስለህጻናት እንክብካቤና ጥበቃ፣ እንዲሁም  ወደ ላቀ ደረጃ እንክብበካቤና የሥነልቡና አገልግሎቶች የሚደረስበትን መንገድ የተመለከተ የመጀመሪያ ደረጃ የሥነ-ልቡና እርዳታ ስልጠና መስጠት ይገባል።
- የገንዘብ ድጋፈን የሚመለከት መረጃ ተደራሽነት እንቅፋቶችን መቅረፍ ይገባል።  የመረጃ ሥርጭት በሁለንተናዊ መርሆች መሠረት ሊዘረጋናና በተቻለ መጠን ሁሉንም አካታችና በብዙ የአቀራረብ ስልቶች (ሞዳሊቲስ) ሊቀርብ  ይገባል። በዕድሜ የገፉ ሰዎች፣ የአካለ ጉዳተኞች፣ የንዑስ ቋንቋ ተናጋሪዎች እና ሌለ\ች የተገለሉ ቡድኖች የገንዘብ ደጋፍ መረጃን ለማግኘት ተግዳሮት ሊኖርባቸው ስለሚችል ተቋርጠው ሊቀሩ ይችላሉ።
- የተጠያቂነት አሠራር መዘርጋት ይገባል። ይህም አሠራር በገንዘብ ድጋፍ አቅራቢው አካል ላይ ብቻ ሳይወሰን ዘርፈ ብዙ ቅሬታዎችና ግብረ መልሶች የሚሰበሰቡበት  መሆን አለበት።
- የግለሰቦችን መረጃ መጠበቅን እና የድጋፍ ተጠቃሚዎችን መረጃ ለ\ምንግስተ እና/ወይም ለግል ዘርፍ አካላት ማካፈል የሚኖረውን ጉዳት  ከግምት ማስገባት፣ በየፕሮግራሞች ዑደት ሁሉ  የግለሰቦችን መረጃ የመጠበቅ መርህን  ማካተት  ያስፈልጋል።

*ለተጨማሪ ቁልፍ ተግባራት  [ERC Tips for Protection in Cash-Based Interventions ](#) እና [GPC-IASC Identifying & Mitigating Gender-based Violence Risks within the COVID-19 Response Tip Sheet](#) ይመልከቱ።*

---

ከዚህ በላይ ከተካተቱት በተጨማሪም፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጠቃሚ ምንጮች ናቸው።

## የገንዘብ ነክ ድጋፍና የከለላ መመሪያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰነዶች

- የገንዘብ ነክ ድጋፍ መመሪያ (Guide for Protection in Cash-based Interventions. Also available in: FR)
- በገንዘብ ነክ ድጋፍ ከለላ ስለመስጠት ጠቃሚ ጥቂማዎች (Tips for Protection in Cash-based Interventions. Also available in: FR)
- ስበገንዘብ ነክ ድጋፍ ከለላ ስለመስጠት ቁልፍ ምክረ ሀሳቦች (Key Recommendations for Protection in Cash-based Interventions. also available in: FR)
- ገንዘብ በሚላክ ፕሮግራም ህጻናትን መታደግ (Child Safeguarding in Cash Transfer Programming)
- ከኮቪድ ለመታደግ ሁለንተናዊ መሥፈርቶች (Sphere Standards for COVID-19 Responses)
- የካሽ ለርኒንግ ፓርትነርሺፕ የፕሮግራም ብቃት መለኪያ ( CaLP's Programme Quality Toolbox)
- የካሽ ለርኒን ፓርትነርሺፕ በገንዘብ ድጋፍ ከለላ መስጠት የቴማቲክ ድረገጽ (CaLP's thematic web page on CVA within the protection sector)

---

- የካሽ ለርኒንግ ፓርትነርሺፕ የገንዘብ ድጋፍና የኮቪድ-19 መመሪያ፤ግዓረብኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛና በስፓንኛ ቅጂዎች ያሉት ( CaLP's live CVA and COVID-19 guidance available in Arabic, English, French and Spanish )
- ከካሽ ለርኒንግ ፓርትነርሺፕ የተገኙ የገንዘብ ድጋፍነ የኮቪድ-19 ጠቃሚ መረጃዎች ጥንቅር( Compilation of CVA and COVID-19 Key Resources from the Cash Learning Partnership (CaLP) )
- የካሽ ለርኒንግ ፓርትነርሺፕ የሥርዓተ ፆታና አካትቶ ድረገጽ (CaLP's thematic webpage on gender and inclusion )
- የገንዘብነ ፆታ ተኮር ጥቃት መረጃ ስብስብ (በእንግሊዝኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በስናንኛ እና በዓረብኛ) (The Cash and GBV Compendium (link includes English, French, Spanish and Arabic. ))
- የገንዘብና ፆታ ተኮር ጥቃት መረጃ ስብስብ ማሰልጠኛ ሥርዐተ ትምህርት (በእንግሊዘኛ፣ በፈርንሳይኛ፣ በስፓንኛ እና በዓረብኛ) (The Cash and GBV Compendium training curriculum in English, French, Spanish and Arabic.)
- የደብሊዩ.አር.ሲ- አይ.አር.ሲ-ሜርሲ ኮርፕስ የገንዘብና ፆታ ተኮር ጥቃት ቱልኪት (በፈረንሳይኛ፣ በእንግሊዝኛና በስፓንኛ) WRC-IRC-Mercy Corps' Cash and GBV Toolkit (French, Arabic and Spanish also available)
- ዓለም ዐቀፍ የከለላ ጉድኝት የፈንጂ መከላከልና የጾታ ተኮር ጥቃት መረጃ ጠቋሚ (GPC Mine Action And Cash-Based Interventions Tip-Sheet)
- የዓለም ዐቀፍ ነፍስ አድን ኮሚቴ የገንዘብ ድጋፍ ማድረጊያ መመሪያዎች- የኮቪድ-19 ድጋፍ እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጀ (IRC's CVA Resources - COVID-19 Adaptation and Response: Adaptation Guidance, Distribution Guidance; and Response Guidance; )
- የዓለም ምግብ ፕሮግራም፣ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ገንዘብ ነክ አላላኮች ( WFP Guidance for Cash-Based Transfers in the Context of the COVID-19 Outbreak)